ስለ ደረሰኝ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ



ግንቦት 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ይዘት

ክፍል አንድ:- አጠቃላይ ሁኔታ

1.1. ዓላማ

1.2. ውጤት

1.3. ወሰን

1.4. ትርጓሜ

ክፍል ሁለት:- ማንዋል ደረሰኝ

2.1 ደረሰኞች

2.2. የደረሰኝ ህትመት ፈቃድ አሰጣጥና የደረሰኝ ይዘት

2.3. የማንዋል ደረሰኝ አጠቃቀም

ይዘት...

2.4. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ለተደረገ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ

2.5. የደረሰኝ ቁጥጥርና አወጋገድ

2.6. ተግባርና ኃላፊነት

2.7. የታክስ ከፋዩ ተጠያቂነት

2.8. የባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያስፈልግ ሊታተሙ የሚችሉ ሰነዶች

2.9. የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ሰነድ

2.10. የንግድ ስም እና ምልክት በደረሰኝ ላይ ስለማካተት

2.11. በቅይጥ አቅርቦት/በታክስ ነፃ ግብይት ወቅት ስለሚኖር አሰራር

ይዘት...

2.12. በሻውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች ሥለሚኖር አሠራር

2.13. የትራንስፖርትና የኢንሹራንስ ድርጅቶች ስለሚጠቀሙበት ደረሰኝ

2.14. በተለያዩ አካላት ስለሚሰጥ ደረሰኝ

2.15. የአስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣቶች

ክፍል ሶስት:- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ

3.1. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ምንድን ነው

3.2. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ዓይነቶች

3.3. ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ታትመው የሚወጡ ሰነዶች

3.4. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ጥቅም

ይዘት...

3.5. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ መጠቀም ያለባቸው

3.6. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ የሌለባቸው 3.7.

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ለመግዛት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

3.8. የሽ.መ.መሳሪያ ተጠቃሚዎች ማወቅ የሚገባው ነገሮች

3.9. የሽ/መ/መሳሪያ አቅራቢ ግዴታዎች

3.10. ተንቀሳቃሽ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ

3.11. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የአድራሻ ለውጥ ለማድረግ መሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

ይዘት...

3.12. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ በአደራ ስለማስቀመጥ

3.13. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የባለቤት ለውጥ

3.14. የሽያጭ ማጠቃለያ ሪፖርት በየቀኑ ማውጣት ስለማይጠበቅባቸው የንግድ መስኮች

3.15. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን ስለማስወገድ

3.16. ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ጋር ተያይዞ የሚጣል ቅጣት

3.17. ከሽ.መ.መሳሪያ ጋር በተገናኘ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ቅጣት

ክፍል አንድ:- አጠቃላይ ሁኔታ

1.1. ዓላማ

- ዋና ዓላማ
  - ሰልጣኞች ስለደረሰኝ እና ሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታክስ አስተዳደሩ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያዎች አንፃር ግንዛቤ ይይዛሉ::
- ዝርዝር ዓላማ
  - የደረሰኝ ዓይነቶችን በመዘርዘር አገልግሎታቸውን ይረዳሉ፤
  - የማንዋል ደረሰኝ ለማሳተም መሟላት ያለባቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች እና ደረሰኞች መያዝ የሚገባቸውን መረጃዎች ይዘረዝራሉ፤

ዝርዝር ዓላማ...

- የታክስ ከፋይ እና የማተሚያ ቤት ኃላፊነትን ይለያሉ፤
- የሽ.መ.መሳሪያን ምንነት፣ታሪካዊ አመጣጥና ጠቀሜታዎችን ይገልጻሉ፤
- በደረሰኝ እና ሽ.መ.መሳሪያ ዙሪያ በአዋጅና በመመሪያ የተደነገጉ ጉዳዮች ቢጣሱ የሚያስከትሉትን አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶችን ይረዳሉ፤

1.2. ውጤት

- የደረሰኝ አጠቃቀም እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚመለከተው ሁሉ ከሕጉ የሚመነጩ ግዴታዎችን በመወጣት መብቶቹን እንዲጠይቅና በአግባቡ እንዲጠቀምባቸው ያስችለዋል፤
- ግብር ከፋዩ የሚያካሂደውን ሽያጭና የሚያገኘውን ገቢ በቀላሉ ለመቆጣጠር፣ የድርጅቱ የውጭ ደንበኞች የድርጅቱን ትክክለኛ የንግድ እንቅስቃሴ እና የሒሳብ አቋም በቀላሉ ለመረዳት እንዲችሉና ድርጅቱ ግብር በማምት እንዳይወሰንበት ለመከታተል ይረዳዋል።

1.3. መሰን

- የሰነዱ ሽፋን
  - የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008፣ ደንብ 407/2009፣ መመሪያ ቁጥር 149/2011፣ መመሪያ ቁጥር 188/2017፣ መመሪያ ቁጥር 114/2008 ደንብ ቁ.139/99፣ መመሪያ ቁጥር 46/1999 እንዲሁም መመሪያ ቁጥር 87/2005።
- የሥልጠና ተሳታፊዎች
  - ሥልጠናው ለግብር ከፋዩ እና በግብር ከፋዩ ዮርጆት ለማሠረ በዮርጆቱ ሠራተኞችና የተረጋገጠላቸው ባለሙያዎች ይ
- የሚወስደው ጊዜ



1.4. ትርጓሜ

- ማንዋል ደረሰኝ ፡- ታክስ ከፋዩ ለታክስ ዓላማ የሚጠቀምበትና በታክስ ባለሥልጣኑ ወይም በሚኒስቴሩ ዕውቅና እና ፈቃድ አግኝቶ በማተሚያ ቤት የታተመ እና ተከታታይ ቁጥር ያለው ሰነድ ነው።
- የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ:- ማለት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለሚገዙ ሰዎች ሽጭ የሚሰጠው የግብይት ማረጋገጫ ሰነድ ሆኖ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ እና ከነዚህ ታክሶች ነፃ ለሆኑ ግብይቶች የሚሰጥ ሰነድ ሲሆን ቦን እና ትኬትን ያካትታል።

- የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ:- ማለት በታክስ ከፋዩ ስም በጥሬ ገንዘብ፤በቼክ ወይም በባንክ ለተከፈሉ ወይም ገቢ ለተደረጉ ከንግድ ሥራው ጋር ላልተገናኙ ሌሎች ገቢዎች ወይም ገዥ ቀደም ሲል በዱቤ የተሸጠለትን ዕቃ ወይም አገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም የሚሰጥ ማረጋገጫ ሲሆን ዕቃ ወይም አገልግሎት ሽያጭ ስለመፈፀሙ የተሰጠ ደረሰኝን አይጨምርም።
- የግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ:- ማለት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ዕውቅና ለተሰጣቸውና ደረሰኝ ሊቀርብላቸው ላልቻሉ ግብይቶች ግዥ ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ በገዥው ተዘጋጅቶ በወጪ ማስረጃነት የሚቀርብ ሰነድ ነው።

- **በግዥው ተይዞ ለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰጥ ደረሰኝ:-** ማለት ታክሱን ቀንሰው የሚያስቀሩ ወኪሎች ታክሱን ቀንሰው ስለማስቀረታቸው የሚሰጥ የማረጋገጫ ሰነድ ነው።
- **የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ:-**ማለት ዕቃ ወይም አገልግሎት በዱቤ ለሚገዙ ሰዎች ሻጭ የሚሰጠው የግብይት ማረጋገጫ ሰነድ ሆኖ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ እና ከነዚህ ታክሶች ነፃ ለሆኑ ግብይቶች የሚሰጥ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝን ያካትታል።

- **የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ፡-** ማለት በገቢዎች ሚኒስቴር ተረጋግጦ ዕውቅና የተሰጠው ሶፍትዌር እንዲጠቀም የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ ገንዘብ ስለመቀበሉ የሚሰ በኮምፒዩተር የተዘጋጀ የሽያጭ ወይም የገንዘብ መቀበያ ሰነድ ነው።
- **ቦን፡-** ማለት በችርቻሮ ደረጃ በርካታ ተጠቃሚዎችን የሚያስተናግድ ወይም መጠኑ ከአስር ብር በታች ለሆነ ግብይት ለገዥ የሚሰጥ እና የአቅራቢውን መረጃ የያዘ ሰነድ ሆኖ ለወጪ ማቀናነስ ዓላማ የማያገለግል ሰነድ ነው።
- **ትኬት፡-** ማለት የሲኒማ አገልግሎት የሚሰጡ፤ባዛር እና ኤግዚቢሽን የሚያዘጋጁ እና የሙዚቃ ኮንሰርት የሚያቀርቡ እንዲሁም የከተማ አውቶብስ ትራንስፖርት እና መሰል አገልግሎት የሚሰጡ አካላት ከተገልጋዮች ለመግቢያ እና ለመጓጓዣ አገልግሎት የሚያስከፍሉት የገንዘብ መጠን በቅድሚያ የታተመበት ደረሰኝ ነው።

- **የቫውቸር ደረሰኝ:-** ማለት በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አወሳሰንመሠረት የተሰጣቸው የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት የተፈቀደላቸው ለቫውቸር ተጠቃዎች ዕቃ ሲሸጡ የሚሰጡት ደረሰኝ ነው።
- **ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለተቀነሰ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ:-**ማለት ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ የፈፀመ ሰው ከክፍያው ላይ ግብር ለተቀነሰበት ሰው የሚሰጥ የክፍያ ማረጋገጫ ሰነድ ነው።
- **የታክስ ዴቢት ሰነድ ወይም የታክስ ክሬዲት ሰነድ:-** ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ማስተካከያ ሲያስፈልገው ለታክሱ በተመዘገበ አቅራቢ ለገዢ የሚሰጥ የክሬዲት ወይም ዴቢት የማረጋገጫ ሰነድ ነው።

- **የጥሬገንዘብመመዝገቢያመሣሪያ**:-ማለት በሽያጭ መደበኛ ደረሰኝ ፋንታ የዕቃዎችን ወይም የአገልግሎቶችን ሽያጭ የሚመዘግብና ለማንበብ ብቻ የሚቻል ማስታወሻን የሚያከማች በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ፕሮግራም የሚደረግ (ቺፕ) የተገጠመለት በሰርኪዩት የተጋገረ ፕሮግራም የሚጠቀም መሣሪያ ነው።
- **የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ**:-ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚተካ ኮምፒዩተራይዝድ የሆነ መሣሪያ ሲሆን የደንበኞቻችን ትዕዛዝ፣ የትዕዛዙን አፈፃፀምና ሂደትና፣ የዴቢትና ክሬዲት ካርድ ሂሳብን የመመዝገብና የመቆጣጠርና የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ተጨማሪ አቅም ያለው መሣሪያ ነው።

ክፍል ሁለት:- ማንዋል ደረሰኝ

2.1. ደረሰኞች

- በሕግ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለባቸው የደረጃ “ሀ” እና “ለ” ግብር ከፋዮች በሙሉ ደረሰኝ የማሳተም ግዴታ አለባቸው።
- የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለባቸው የደረጃ “ለ” ግብር ከፋይ ሆነው ነገር ግን የሂሳብ መዝገብ መያዝ እስከፈለጉ ድረስ የሕጉን አግባብ ተከትለው ደረሰኝ ማሳተም ይኖርባቸዋል።
- የገቢ ግብር ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሰው ገቢ የማድረግ ኃላፊነት በሕግ የተጣለባቸው ወኪሎች ደረሰኝ ማሳተም ይኖርባቸዋል።

2.2. ተቀባይነት ስለሚኖረው ደረሰኝ

- የተፈቀደና የተመዘገበ፤
- የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጠው ማተሚያ ቤት የታተመ (በ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የታተመ)
- በታክስ ባሥልጣኑ ዕውቅና ከተሰጠው ማተሚያ ቤት ወይም በገንዘብ ሚኒስቴር የታተመ
- ፈቃድ አግኝቶ የሚታተም ደረሰኝ ልዩ መለያ ያካተተ(QRC) መሆን አለበት

2.3 የማንዋል ደረሰኝ ህትመት ፈቃድ ለማግኘት ማሟላት ያለበት ቅድመ-ሁኔታ

- በኢንቨስትመንት ሂደት ላይ ያለና የንግድ ሥራ ያልጀመረ ሲሆን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለተቀነሰ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ ለማሳተም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የኢንቨስትመንት ሰርተፊኬት፤
- ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ለተቀነሰ ንግድ ትርፍ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ ለማሳተም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤
- በንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ታክስ ከፋይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ሕጋዊ የንግድ ሥራ ፈቃድ እና የምዝገባ ምስክር ወረቀት (ሰርተፊኬት)፤

ቅድመ-ሁኔታ...

- የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላወጣና የመደበኛ ሽያጭ ያልጀመረ ሰው የሙከራ ምርት ለመሸጥ ወይም ከግንባታ ሥራ የተረፈ ዕቃ ለመሸጥ የሚያገለግል ደረሰኝ ለማሳተም ምክንያቱን የሚገልፅ ደብዳቤ በተጨማሪነት ማቅረብ ይኖርበታል።
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ወኪል የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማቅረብ አለበት፤

ቅድመ-ሁኔታ...

- የንግድ ምልክት እንዲካተት ጥያቄ ያቀረበ ከኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የንግድ ምልክቱ የተመዘገበበትን ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤
- በሚታተመው ደረሰኝ ላይ የንግድ ስም እንዲጠቀስ በሚፈለግበት ጊዜ የንግድ ስም ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ፤
- ለማሳተም የሚፈልገውን የማንዋል ደረሰኝ ዓይነትና ብዛት ከደረሰኝ ናሙናው ጋር በደረሰኝ ህትመት መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ ላይ በመሙላት ታክስ ለሚከፈልበት ቅ/ጽ/ቤት ማቅረብ አለበት።

2.4. ማንዋል ደረሰኝ ሊይዘው የሚገባው ዝርዝር መረጃ

- **የአቅራቢው ሙሉ ስም፣** አድራሻና የተመዘገበ የንግድ ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ተመዝጋቢ ከሆነ) ቁጥሩና ለታክሱ የተመዘገበበት ቀን እና የደረሰኙ ተከታታይ ቁጥር አስቀድሞ የታተመበት (Pre-Printed)፤
- **የገዥው ሙሉ ስም፣** አድራሻና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መመዝገቢያ፣ የተሸጠው ዕቃ ወይም የተሰጠው አገልግሎት ዓይነትና የገንዘብ መጠን አንዲሁም በሽያጭ ፖሊሲ ወይም በውል ምክንያት የተደረገ የሽያጭ ቅናሽ ገንዘብ መጠን የሚገለፅበት ክፍት ቦታ ያለው፤

ደረሰኙ መያዝ የሚገባው...

- ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ የሚፈለገውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ከተ.ዕ ታክስ ነጻ የገንዘብ መጠን፣ በፊደል እና በአሃዝ የተፃፈ ጠቅላላ የሽያጭ/ግብይት ዋጋ የገንዘብ መጠን እንዲሁም ደረሰኙ የተሰጠበት ቀን የሚገለፅበት ክፍት ቦታ ያለው፤
- ደረሰኙን ያዘጋጀው ወይም ገንዘቡን የተቀበለው ሠራተኛ ስምና ፊርማ የሚሰፍርበት ክፍት ቦታ፤
- የደረሰኝ አታሚው ስም፣ መለያ ቁጥር፣ ደረሰኙ የታተመበት ቀንና የአታሚው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቁጥር እና የአታሚው ስልክ ቁጥር እንዲሁም የሽያጭ ደረሰኙ እንዲታተም በባለሥልጣኑ የተፈቀደበትን ደብዳቤ ቁጥርና ቀን አስቀድሞ የታተመ፤

2.5. የማንዋል ደረሰኝ ህትመት ፈቃድ አሰጣጥ እና አጠቃቀም

- ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች የሚነግድ ወይም ቤት የሚያከራይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ግለሰብ በእያንዳንዱ ክልል/ከተማ አስተዳደር ለሚያከናውነው ግብይት የሚሰጠው ደረሰኝ ዋና ምዝገባ ባከናወነበት ክልል/ከተማ አስተዳደር በሚገኘው የታክስ ባለሥልጣን/ በገቢዎች ሚኒስቴር ብቻ የተፈቀደና በአንድ አታሚ የታተመ መሆን አለበት።

- የህትመት ፈቃድ የሰጠው አካል (ታክስ ባለሥልጣን) ለታክስ ከፋዩ የፈቀደውን የደረሰኝ ዓይነትና ብዛት ታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራውን ለሚሠራባቸው ወይም ቤት ለሚያከራይባቸው ሌሎች ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች መረጃውን በቋሚነት መላክ አለበት።

ፈቃድ አሰጣጥ እና አጠቃቀም...

- ከአንድ በላይ የንግድ ሥራ ዘርፍ እና የንግድ አድራሻ ያለው ታክስ ከፋይ አሳትሞ በሚጠቀምበት ደረሰኝ ላይ ሁሉንም ዘርፎች እና አድራሻቸው ተጠቃሎ መታተም ይኖርበታል።
- ታክስ ከፋዩ በተለያየ ቦታ ለሚገኝ ገቢ መሰብሰቢያ እንዲውል ተከፋፍሎ የሚሰራጭ የማንዋል ደረሰኝ ጥራዝ ዝርዝር ስርጭቱ እንደተከናወነ የደረሰኝ ህትመት ፈቃድ ለሰጠው የታክስ ባለሥልጣን በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።
- የህትመት ፈቃድ የሰጠ አካል ታክስ ከፋዩ ስለተሰራጨው የማንዋል ደረሰኝ ጥራዝ ዝርዝር ያቀረበለትን መረጃ የንግድ ሥራው ለሚሠራባቸው የፌደራል፣ የክልል/የከተማ አስተዳደር ታክስ ባለሥልጣናት በቋሚነት መላክ አለበት።

2.6. የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ የአጠቃቀም ፈቃድ አሰጣጥ

- የሽ.መ.መሳሪያ መጠቀም የሚያችል ታክስ ከፋይ የታክስ ባለሥልጣኑን በማስፈቀድ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ መጠቀም ይችላል።
- በኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ መጠቀም የሚፈልግ ታክስ ከፋይ በሽ.መ.መሳሪያ መጠቀም የማይችልበትን አሳማኝ ምክንያት ገልፆ ጥያቄውን ታክስ ለሚከፍልበት የታክስ ባለሥልጣን በጽሑፍ ማቅረብ አለበት።
- ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩን የኮምፒዩተር ፕሮግራም ሶፍትዌሩን የሠራውን ሰው ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና ሕጋዊ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲያቀርብ በማድረግ ጥያቄው በቀረበ በ10 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ መግለፅ ይኖርበታል።

❑ በኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ለመጠቀም ፈቃድ የሚሰጠው፡-

- በኮምፒዩተር ፕሮግራም አማካኝነት የሚታተመው ደረሰኝ ቢያንስ በደረሰኝ ናሙና ላይ የተመለከቱትን መረጃዎች የሚይዝ ሆኖ ሲገኝ እና
- ለታክስ መረጃ ጥቅም ላይ የሚውል መረጃ እንደማይቀር ለማረጋገጥና ተከታታይ የሆነ የደረሰኝ ቁጥር ለማተም በሚያስችል አኳኋን የተዘጋጀ የኮምፒዩተር ፕሮግራም መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

2.7. የማንዋል ደረሰኝ አጠቃቀም

2.7.1 ከሽ.መ.መሳሪያ ውጪ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ

- የሽ.መ.መሳሪያው ሲበላሽ ወይም ለእድሳት በተላከ ጊዜ ወይም የኤሌክትሪክ ኃይል በሚቋረጥበት ጊዜ ለሚከናወን ሽያጭ የማንዋል ደረሰኝ መሰጠት አለበት።

2.7.2. ቦንና ትኬት የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች

- በችርቻሮ ደረጃ ሽያጭ የሚያከናውኑ ግብር ከፋዮች የሽ.መ.መሳሪያ ሲበላሽ/ለእድሳት ሲላክ ወይም የኤሌክትሪክ ሀይል በሚቋረጥበት ጊዜ በታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድ በታተመ ቦን መጠቀም አለባቸው።
- በተለያየ የንግድ ዘርፍ የተሠማራ ታክስ ከፋይ በአንድ ጊዜ ለሚያከናውነው ግብይት የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም /ከታክስ ነፃ የሆነ ግብይት ጠቅላላ ዋጋ ከ10 ብር የማይበልጥ ከሆነ በታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድ በታተመ ቦን መጠቀም አለበት።


ቦንና ትኬት የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች...

- የሂሳብ መዝገብ መያዝ ያለበት ታክስ ከፋይ የተቀበለውን ቦን ለግዥው ማረጋገጫ/ለታክስ ማቀናነሻ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ለግብይቱ መቀበል ያለበት የማንዋል ደረሰኝ ብቻ ነው።
- ባዛር/ኤግዚቢሽንና/የሙዚቃ ኮንሰርት የሚያዘጋጁ ታክስ ከፋዮች በባለስልጣኑ ፈቃድ የታተመ ትኬት መጠቀም የሚችሉት የሽ.መ.መሳሪያው ሲበላሽ/በእድሳት ላይ ሲሆን/ኤሌክትሪክ በሚቋረጥበት ጊዜ ብቻ ይሆናል።

ቦንና ትኬት የሚሰጥባቸው....

- ቦን እና ትኬት የሚጠቀሙ ታክስ ከፋዮች የየዕለቱን ሽያጭ በማጠቃለል እንደአግባብነቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ፣ ወይም የታክስ ነፃ ግብይት ደረሰኝ መቁረጥ ያለባቸው ሲሆን የቦን እና የትኬቱን ቁጥር በደረሰኞቹ ላይ በመመዝገብ መወራረስ አለበት።
- በአዲስ አበባ ከተማ የሚሰጠው ትኬት በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የመዝናኛ ግብር መሠረት የህዝብ መዝናኛ በሆነ ስፍራ ለመግባት በመግቢያ ዋጋ ላይ የሚከፈለው 10 በመቶ የመዝናኛ ግብር ተከፍሎበት ሳይመዘገብና የታክስ ባለሥልጣኑ ማህተም ሳያርፍበት አገልግሎት ላይ መዋል የለበትም።

ቦንና ትኬት የሚሰጥባቸው....



ቦን(BON)

ብዛት Qty	የእቃው ዓይነት Description	የአንዱ ዋጋ Unit Price	ጠቅላላ ዋጋ Total Amount

የደረሰኝ ቁጥር — Invoice No
ቀን — Invoice Date
የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር — TIN
የተ.እ.ታ.ቁጥር — VAT NO
የታተመ Per-printed
ድምር /total/
ተ.እ.ታ /VAT 15%/
በፊደል ብር IN Word
የገዢው ተቀባይ ፈርማ — Cansar's Signature
ስርጭት Distribution
ዋናው ለከፋይ Original Customer
2ኛ ኮፒ ለሂሳብ ክፍል 2nd Copy Accounts
3ኛ ኮፒ ለማደራጃ 3rd Copy pad
ማሳሰቢያ፡- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ በማይሠራበት ጊዜ እና ታክስ ከፋይ ላልሆኑ ንግዶች ሽያጭ ለሸማቹ ብቻ ሊሰጠው ቀኝም ላይ የሚውል ነው።

ትኬት (Ticket)

የድርጅቱ ስም —— Taxpayer Name
የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር —— TIN
ቫት (VAT) 15% ጨምሮ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ
በማይጠቀሙበት ጊዜ ብቻ የሚያገለግል)

ቁጥር ——
NO
የመግቢያ ዋጋ ብር —— ENTRANCE FEE Birr
ቦ ——
ንጽጽ

ዝርዝር ሚኒስቴር ፀ——ቅጽሽት ቁ-ቀን----ወር---- ዓ.ም. በቁጥር ——— በቀሃፊ ደብጻቢ እንዲታዮም ተፈቅዶ የታተመ፣
ግብሚያ ድርጅቱ ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የብቅት የረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቁጥር

ማሳሰቢያ፡- የድርጅቱ ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የትኬት ዋጋ እና የመግቢያ ዋጋ የታተመበት (pre-printed) መሆን አለበት።

2.7.3 የግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ

- የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ታክስ ከፋይ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ከሌለባቸው ጋር ለሚደረገው ግብይት ከታክስ ባለሥልጣኑ በማስፈቀድ የወጪ ማስረጃ የግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ በማሳተም መጠቀም አለበት።
- የግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ የሚያሳትም ታክስ ከፋይ የሚያሳትመው ደረሰኝ ከመታተሙ በፊት የተፈቀደና የተመዘገበ እንዲሁም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለው እና በታክስ ባለሥልጣኑ ዕውቅና በተሰጠው ማተሚያ ቤት/በገንዘብ ሚኒስቴር የታተመ ወይም እንዲታተምና ጥቅም ላይ እንዲውል የተፈቀደ ከሆነ ልዩ መለያ /Security feature/ እንዲያካትት አይገደድም።

የግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ...

- የግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ መጠቀም የሚቻልባቸው ግብይቶች፤
  - ደረሰኝ መስጠት የማይችሉ በአነስተኛ ወይም በችርቻሮ ደረጃ ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ሲሆን:-
  - ከደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ላይ የቤት ኪራይን ጨምሮ የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ ሲፈጽሙ፣
  - የትራንስፖርት ተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት፣
  - የንግድ ሥራ ካቋረጠ ሰው የሚገዛ የንግድ ሥራ ሀብት፣
  - በሰው ጉልበት የሚሠራ የጫኝና አውራጅ አገልግሎት

የግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ...

- ከላይ የተገለፁት ግብይቶች ስለመፈፀማቸው የሚያረጋግጡ የውል ሰነድ ወይም በግዥ ማረጋገጫ ደረሰኙ ላይ የሻጩን ስም፣ አድራሻ፣ የያዘ መሆን ያለበት ሲሆን የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ከሆነ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩ መመዝገብ አለበት።

- በፈቃድ ሰጪ ተቋማት የማምረት ፈቃድ ወስደው በአነስተኛ ደረጃ ከሚያመርቱ አምራቾች ላይ ለሚፈፀም ግዥ በግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ ግዥ መፈጸም አይቻልም።

2.7.4. የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ

- ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ውጪ የተገኘ ሌላ ገቢ ሲኖር
- ማንኛውም በጥሬ ገንዘብ፣ በቼክ/በባንክ በታክስ ከፋዩ ስም ለተከፈለ ክፍያ፤
- እንዲሁም የዱቤ ግብይት ተከናውኖ ሻጭ ክፍያ በሚቀበልበት ወቅት የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ተቆርጦ መሰጠት አለበት።
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ታክስ ከፋይ ከዕቃ ወይም አገልግሎት ግብይት የቅድሚያ ክፍያ ሲቀበል የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መስጠት ይኖርበታል::

2.7.5. በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ

- የተጨማሪ እሴት ታክስን ይዘው በማስቀረት ለታክስ ባለሥልጣን ገቢ እንዲያደርጉ ውክልና የተሰጣቸው መንግሥታዊ ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች ባለ 4 ዲጂት የሆነ መለያ ልዩ ኮድ ያለው ደረሰኝ ህትመት ፈቃድ በመውሰድ አሳትመው መጠቀም አለባቸው።
- በተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ሥርዓት (IFMIS) የሚጠቀሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ቀንሰው ለሚያስቀሩት የተጨማሪ እሴት ታክስ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ታትሞ የሚወጣውን ደረሰኝ ይጠቀማሉ።

2.8. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ለተደረገ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ

2.8.1. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ስለሚሰጥ ደረሰኝ

- ለሚከተሉት ግብይቶች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ታክስ ቀንሶ የሚያስቀር ግብር ከፋይ ቀንሶ ላስቀረው ታክስ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት:-

  - ለተቀጣሪው ከሚከፈል ክፍያ ላይ የሥራ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሠራተኛ ቀጥሮ የሚያሠራ፤
  - ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ወይም የኪራይ ገቢ ግብር ቀንሶ እንዲያስቀር ኃላፊነት የተሰጠው ሰው፤
  - በአገልግሎት ተቀባዩ/በገዢው ተቀንሶ የሚከፈል የሠንጠረዥ "መ" ታክስ የሚከፍል እና
  - ለንዑስ ሥራ ተቋራጭ የአገልግሎት ክፍያ የሚፈፅም በማዕድን ሥራ የተሠማራ ኩባንያ።

2.8.2. በሀገር ውስጥ የዕቃ/አገልግሎት ግዢዎች ክፍያ ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት የሚሰጥ ደረሰኝ ዓይነትና ስለ ፊቃድ አሰጣጥ

- ባለበጀት መሥሪያ ቤት ቀንሶ ለሚያስቀረው ግብር የሚሰጠው ደረሰኝ የሚታተመው የፌደራል መንግሥት ከሆነ በገንዘብ ሚኒስቴር ሲሆን የክልል/የከተማ አስተዳደር ከሆነ ደግሞ በገንዘብና ኢኮኖሚ ቢሮ ነው።
- በተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ሥርዓት (IFMIS) የሚጠቀሙ የመንግስት መ/ቤቶች ለሚያከናውኑት ግብይት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ታትሞ የሚወጣውን ደረሰኝ ይጠቀማሉ።
- የመንግሥት ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች ለሻጩ ከሚከፈል ሂሳብ ላይ ቀንሰው ለሚያስቀሩት የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰጡት ደረሰኝ በታክስ ባለሥልጣኑ ፊቃድ የሚታተም ይሆናል።

የቀጠለ...

- የንግድ ትርፍ ግብር እና የኪራይ ገቢ ግብር ቀንሰው የሚያስቀሩ ሌሎች ሰዎች ቀንሰው ለሚያስቀሩት ግብር የሚሰጡት ደረሰኝ የሚታተመው በባለሥልጣኑ ፈቃድ መሠረት ነው።
- በንግድ ሥራ ያልተሠማሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራትና የሃይማኖት ተቋማት የቀ.ተ.እ.ታ ክስ የሚከፈልበት ገቢ የሚያስገኝ ሥራ በቋሚነት ወይም አልፎ አልፎ የሚያከናውኑ ከሆነ በታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድ የታተመ ደረሰኝ መጠቀም አለባቸው።

2.8.3. ግብርን ቀንሰው ሲያስቀሩ ደረሰኝ መስጠት የማይገደዱ

- የመንግሥት ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች
- በትራንስፖርት ንግድ ሥራ የተሠማራ ሰው ለሹፌርና ለረዳት ደመወዝ ሲከፈል።
- ሌሎች ቀጣሪዎች ተቀጣሪው ደረሰኝ እንዲሰጠው ሲጠይቅ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሲሆን በዓመቱ መጨረሻ ለእያንዳንዱ ሠራተኛ በዓመት የተከፈለውን ክፍያ ያጠቃለለ ደረሰኝ መስጠት አለበት።



ሙከራ አንድ

- የማንዋል ደረሰኝ ህትመት ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች ዘርዝሩ?
- የደረሰኝ ዓይነቶችን በመዘርዘር አገልግሎታቸውን ግለጹ?

2.9. የደረሰኝ ቁጥጥርና አወጋገድ

2.9.1. ስለ ደረሰኝ መጥፋት ወይም ከጥቅም ውጪ መሆን

- ታክስ ከፋዩ ያሳተመው ደረሰኝ የጠፋው ወይም ከጥቅም ውጪ የሆነው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።
- ማስረጃ መቅረብ ያለበት ከፖሊስ ጣቢያ፣ ከፍርድ ቤት ወይም ከእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ ኤጀንሲ እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ይሆናል።
- ደረሰኙ መጥፋቱ/ከጥቅም ውጪ መሆኑ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ በጋዜጣ እና ቴሌቪዥን/ሬዲዮ ማስታወቂያ ማስነገር ይኖርበታል።

መጥፋት ወይም ከጥቅም ውጪ መሆን...

- ለማስታወቂያ ክፍያ የተፈፀመበት ደረሰኝ በ10 ቀን ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት።
- ባለሥልጣኑ ማስረጃው ሲቀርብለት ደረሰኙ ያልተሠራበት ስለመሆኑ የሚገልፅ ማረጋገጫ ይሰጣል።
- ደረሰኙ በማንኛውም ሁኔታ ጥቅም ላይ አለመዋሉን ማረጋገጥ ካልተቻለ ደረሰኙ ጥቅም ላይ እንደዋለ ይቆጠራል።
- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለተቀነሰ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ እና የግዥ ማረጋገጫ ሰነድ በተለያየ ምክንያት ሲጠፋ/ከጥቅም ውጭ ሲሆን ደረሰኙ ስለመጥፋቱ በብዙሃን መገናኛ ማስታወቂያ ማስነገር ሳያስፈልገው ለታክስ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል።

2.9.2. ጥቅም ላይ የማይውል ደረሰኝ ስለመሰረዝ

- ታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራውን ሲያቋርጥ ወይም የዘርፍ፣ የአድራሻና የስም ለውጥ ሲያደርግ ታትመው ጥቅም ላይ የዋሉ ደረሰኞችን እንዲሰረዙ ማድረግ አለበት።
- ታክስ ከፋዩ ዘርፍ የቀነሰ እንደሆነ በእጁ ላይ ያለው ደረሰኝ ሳይሰረዝ የንግድ ሥራውን ለቀጠለበት ዘርፍ ጥቅም ላይ እንዲውል በታክስ ባለሥልጣኑ ሊፈቀድ ይችላል።
- የንግድ ሥራውን ያቋረጠ ታክስ ከፋይ የንግድ ሥራው ከተቋረጠ እና ደረሰኙን ከመለሰ በኃላ ለሚቀበላቸው ተሰብሳቢ ሂሳቦች አስቀድሞ ታክስ ይከፍልበት ለነበረው ቅ/ጽ/ቤት ለግብይቱ ማረጋገጫ የሚሆን ደብዳቤ እንዲፃፍለት ሊጠይቅ የሚችል ሲሆን ቅ/ፅ/ቤቱም የግብይቱን ዋጋ እና ቀን የሚያሳይ ደብዳቤ ለከፋዩ በአድራሻው መላክ አለበት።

- ፈቃድ እና ዕውቅና ያልተሰጣቸውን ደረሰኞች አለመጠቀም፤
- ለአንድ ግብይት ጥቅም ላይ የዋለን ደረሰኝ ለሌላ ግብይት አለመጠቀም፤
- በበራሪና ቀሪ ቅጠሎች ላይ የተለያየ መረጃ አለመመዝገብ፤
- ያለደረሰኝ ሽያጭ አለማከናወን
- ግብይቱ ከተከናወነበት ሽያጭ ዋጋ የተለየ የገንዘብ መጠን በደረሰኙ ላይ አለማስፈር፤
- የደረሰኝ ህትመት ከተፈቀደለት ግብር ከፋይ ውጪ ለሌላ ታክስ ከፋይ ጥቅም ላይ እንዲውል አለማድረግ፤

የታክስ ከፋይ ኃላፊነት...

- ደረሰኝ ለሚጠይቁ ግዥ ፈፃሚዎች ሽያጭ አለመከልከል፤
- ተመሳሳይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ በማሳተም ጥቅም ላይ አለማዋል፤
- እንዲሰረዝ ውሳኔ በተሰጠበት ደረሰኝ አለመጠቀም፤
- ደረሰኞች መያዝ ያለባቸውን ዝርዝር መረጃዎችን ያሟሉ ደረሰኞችን አሳትሞ መጠቀም፤
- በራሪና ቀሪ ቅጠሎች ያለው ደረሰኝ ማሳተም፣ በጥንቃቄ መያዝ እና ግብይት የተፈጸመባቸውን ደረሰኞች መያዝ እስካለባቸው ጊዜ ድረስ ይዞ ማቆየት፣ እንዲቀርብ ሲጠየቅ ማቅረብ፤
- የደረሰኝ አጠቃቀም መከታተያ ሌጀር ለሁሉም በግልጽ በሚታይበት ቦታ መስቀል እና ትክክለኛ መረጃ እንዲይዝ ማድረግ፤

የታክስ ከፋይ ኃላፊነት...

- የሽ.መ.መሳሪያ መጠቀም ሳይችል ሲቀር ህጋዊ የሆነ የሽያጭ ደረሰኝ መስጠት፤
- የደረሰኝን 2ኛ ቅጂ ለሒሳብ ክፍል ማስተላለፍ እና ከማመሳከሪያ ሰነዶች ጋር ማያያዝ፤
- በደረሰኝ ላይ በስህተት ሲፃፍ ደረሰኙን ቮይድ በማድረግ ሶስቱንም የደረሰኝ ቅጠሎች ባንድ ላይ አስሮ በጥራዙ ውስጥ ማስቀመጥ።
- ያሳተመውን ደረሰኝ በቅደም ተከተል መጠቀም፤ በተለያየ አካባቢ ወይም በተለያየ የንግድ ዘርፍ ለሚጠቀምባቸው ደረሰኞች የደረሰኝ ቅደም ተከተል ተፈፃሚ የሚሆነው ለየንግድ ቦታው ወይም ዘርፉ የተከፋፈሉትን ደረሰኞች መሠረት አድርጎ ይሆናል።
- የደረሰኝ አጠቃቀም መከታተያ ሌጀር ለሁሉም በግልጽ በሚታይበት ቦታ መስቀል እና ትክክለኛ መረጃ እንዲይዝ ማድረግ፤

2.10.2. የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ የሚጠቀም ታክስ ከፋይ ኃላፊነት

- በሶፍትዌር ከመጠቀሙ በፊት የሶፍትዌር ፕሮግራሙን ያለማውን ሰው ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ እና የሶፍትዌር ፕሮግራሙን ማቅረብ አለበት።
- የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ እንዲጠቀም የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ የተጠቀመበትን የሽያጭ ወይም የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ብዛትና ቁጥር በመግለጽ በየሩብ ዓመቱ ታክስ ለሚከፍልበት ቅ/ጽ/ቤት ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

2.10.3. የማተሚያ ቤት ኃላፊነት


- ለታክስ ዓላማ የሚውል ደረሰኝ ለማተም የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመያዝ፤
- የደረሰኞቹን ዓይነትና መጠን በባለሥልጣኑ የተመዘገቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።
- ከባለሥልጣኑ ደብዳቤ የተፃፈለት መሆኑን
- የህትመት ጥያቄውን ያቀረበው ሰው ታክስ ከፋዩ ራሱ ወይም ወኪሉ መሆኑን የማረጋገጥ
- በቀረበለት የደረሰኝ ናሙና ላይ ደረሰኝ እንዲታተም ፈቃድ የሰጠው የታክስ ባለሥልጣን ማህተም መኖሩን ማረጋገጥ።

የማተሚያ ቤት ኃላፊነት...

- በቀረበለት ደረሰኝ ናሙና ላይ የተመለከቱ መረጃዎች በሚታተመው ደረሰኝ ላይ እንዲካተቱ ማደረግ፤
- የደረሰኞቹን ቁጥር ተከታታይነት የማረጋገጥና ምስጢራዊ መለያ ሰጥቶ የማተም እንዲሁም በማንኛውም ሁኔታ ተመሳሳይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ በድጋሜ እንዳይታተም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ፤
- የደረሰኝ ህትመት ጥራትን የማሟላት፤
- የህትመት አገልግሎት የተሰጣቸውን ታክስ ከፋዮች ዝርዝር የያዘ ሪፖርት በየሩብ ዓመት (በየሦስት ወሩ) ታክስ ለሚከፍልበት ቅ/ጽ/ቤት የማቅረብ፤

የማተሚያ ቤት ኃላፊነት...

- የህትመት አገልግሎት የሚሰጥበትን አድራሻ ሲቀይር ታክስ ለሚከፍሉበት ቅ/ጽ/ቤት የማሳወቅ ግዴታ፤
- ለማተሚያ ቤቱ ክፍያ ሲፈፀምለት በሚሰጠው ደረሰኝ ላይ የታተመውን ደረሰኝ ዓይነትና ሴሪያል ቁጥር (ከ...እስከ) የመስጠት ግዴታ አለበት።



ሙከራ ሁለተ

- የማንዋል ደረሰኝ የሚጠቀም ታክስ ከፋይ እና ማተሚያ ቤት ኃላፊነትን ዘርዝሩ?

2.11. የታክስ ክፋዩ ተጠያቂነት

- ያሳተመውን ደረሰኝ በትውስት/በሽያጭ/በማንኛውም መልክ ለሶስተኛ ወገን እንዲጠቀምበት አሳልፎ የሰጠ እንዲሁም በደረሰኙ በራሪና ቀሪ ላይ የተለያየ የገንዘብ መጠን አስፍሮ የተገኘ እንደሆነ፤
- ግብይት ሳይኖር ግብይት እንደተፈፀመ በማስመሰል ለ3ኛ ወገን የሰጠ
- በግብይት ወቅት ፈጽሞ ደረሰኝ ያልሰጠ እንደሆነ፤
- ደረሰኝ ለሚጠይቁ ገዢዎች ሽያጭ ወይም ደረሰኝ የከለከለ እንደሆነ

እንደሁኔታው በታክስ አስተዳደር ወይም በታክስ ወንጀል ተጠያቂ ይሆናል።

2.12. የባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያስፈልግ ሊታተሙ የሚችሉ ሰነዶች

- የዕቃ ማስተላለፊያ ሰነድ /Delivery Order/፣
- የዋጋ ማቅረቢያ ኢንቮይስ /Proforma invoice/፣
- የዋጋ መጠየቂያ ቢል (Payment request Bill)፣
- ድርጅቶች ለውስጥ ቁጥጥር የሚጠቀሙባቸው እንደ የገንዘብ ወጪ ማዘዣ ደረሰኝ (payment voucher)

የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ማስተካከያ ሲያስፈልገው ለታክሱ በተመዘገበ አቅራቢ ለገዢ የሚሰጥ የክሬዲት ወይም ዴቢት የማረጋገጫ ሰነድ ሲሆን በታክስ ባለስልጣኑ ፈቃድ የሚታተም ይሆናል።

3.10. የንግድ ስም እና ምልክት በደረሰኝ ላይ ስለማካተት

ደረሰኝ የሚያሳትሙ ታክስ ከፋዮች በሚያሳትሙት ደረሰኝ ላይ የንግድ ስም ወይም የንግድ ምልክት እንዲካተትላቸው ሊፈቅድ ይችላል።

2.14. በቅይጥ አቅርቦት ወይም በታክስ ነፃ ግብይት ወቅት ስለሚኖር አሰራር

- የተጨማሪ እሴት ታክስ መሰብሰብ የሚጠበቅበት ከታክስ ነፃ የተደረገና ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የሚያከናውን ከሆነ ለሁለቱም የግብይት ዓይነቶች እንደ አግባብነቱ የተ.እ.ታ ወይም ከታክስ ነፃ ደረሰኝ መስጠት አለበት።
- ከታክስ ነፃ ለሆነ ግብይት የሚሰጠው ደረሰኝ ዜሮ ታክስ የሚያሳይ መሆን አለበት።
- ሙሉ በሙሉ ከተ.እ.ታ ወይም ከተ.ኦ.ታ. ነፃ የሆነ ግብይት ብቻ የሚያከናውን ታክስ ከፋይ ከሆነ ከታክስ ውጪ የሆነውን የሽያጭ ደረሰኝ በናሙናው መሠረት አሳትሞ የሚጠቀም ይሆናል።

2.15. በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች ሥለሚኖር አሠራር

- የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ አምራቾች፣ ላኪዎችና ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች ለቦንድድ ግብዓት አቅራቢዎች የተ.እ.ታ. ክፍያ መፈፀም ሳያስፈልጋቸው ግብዓት በሚገዙበት ጊዜ ከሻጭ በተሰጣቸው ደረሰኝ የተገለፁትን ግብዓቶች ከተፈቀደላቸው የቫውቸር ደብተር ላይ እንዲቀናነስ ይደረጋል።

2.16. የትራንስፖርትና የኢንሹራንስ ድርጅቶች ስለሚጠቀሙበት ደረሰኝ

- በትራንስፖርትና ኢንሹራንስ ዘርፍ የተሠማሩ የደረጃ “ሀ” እና “ለ” ግብር ከፋዮች ደረሰኝ አሳትመው ለመጠቀም ጥያቄ ካቀረቡ የደረሰኝ ህትመት ፈቃድ ይሰጣቸዋል።

5.2. የቫውቸር ሥርዓት የጉምሩክ የአሠራር ስርዓት

ሀ. ትርጉም

የቫውቸር ሥርዓት የጉምሩክ የአሠራር ስርዓት ማለት ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆኑ የሚያስችል የምስክር ወረቀት ለተሰጣቸው ተጠቃሚዎች በቫውቸር ደብተር አመካኝነት ያስገቡት ወይም ከቦንድድ የግብዓት አቅርቦት መጋዘን የገዙት ጥሬ ዕቃን በመጠቀም የተመረተ ምርት በግብዓት ምርት ጥመርታ መሠረት ወደ ውጪ የተላከ ስለመሆኑ የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት ማለት ነው።

ለ. የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

አምራች ላኪዎች

ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች እና

ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች ናቸው

የቀጠለ...

5.2.1. የቫውቸር ደብተር የሚሰጥበት የጉምሩክ የአሠራር የሥራ ሂደት

ሀ/ትርጉም፤

ይህ የጉምሩክ አሰራር የስራ ሂደት በቫውቸር ስርዓት ለሚገቡ ጥሬ እቃዎች ወይም አላቂ ምርት መገልገያ እቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሁኖ በሚገቡበት ግዜ የቀረጠና ታክስ መጠኑ እንደ እዳ የሚመዘገብበት ደብተር የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ነው።

ለ/ የቫውቸር ደብተር ለመስጠት ሊሟሉ የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች

ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጠ የሥርዓቱ ተጠቃሚነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣

ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተፃፈ ደብዳቤና የግብዓት ምርት ጥምርታ

ተጠቃሚው የሚያቀርበው ማመልከቻ

የድርጅቱ ተወካይ የውክልና ደብዳቤና መታወቅያ

ለጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች የሽያጭ ውል ስምምነት

2.17. በተለያዩ አካላት ስለሚሰጥ ደረሰኝ

- የመንግሥት ባለበጀት መሥሪያ ቤት ፈቃድ በሰጠበት/ክትትልና ድጋፍ በሚያደርግበት ዘርፍ ለተመዘገቡ ታክስ ከፋይ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በማሳተም እንዲያሰራጩ/የህትመት ፈቃድ እንዲሰጥ በሚኒስቴሩ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።
- ውክልና የተሰጠው መ/ቤት የህትመት ፈቃድ የሚሰጥበትን ምክንያት በጽሑፍ በመግለፅ ጥያቄውን ማቅረብ እንዲሁም የሚጠቀምበትን የደረሰኝ ዓይነትና ይዘት ናሙና ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት።
- የቴምብር ቀረጥ እንዲሰበስቡ ውክልና የተሰጣቸው አካላት ቀረጡን ሲሰበስቡ የሚሰጡት ደረሰኝ ተቀባይነት ይኖረዋል።

2.18. የአስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣቶች

2.18.1 የአስተዳደራዊ ቅጣት

- ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለገዥ ባልሰጠው በእያንዳንዱ ደረሰኝ 50ሺ. ብር ቅጣት ይቀጣል።
- አስተዳደራዊ ቅጣት የገንዘብ መቀጮ ብቻ አይደለም። የሚከተሉትም በአስተዳደራዊ ውሳኔ የሚጣሉ መቀጫዎች ናቸው።
- ✓ የንግድ ድርጅትን /መደብርን/ ማሸግ፣
- ✓ ፈቃድ ማገድ፣
- ✓ ፈቃድ መሰረዝ እና
- ✓ ሌሎችንም ያካትታል።

2.18.2 የወንጀል ቅጣት

I. የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ያዘጋጀ፣ ያተመ፣ የሸጠ/ያሰራጨ/የታክስ ዕዳውን ለመቀነስ/ተመላሽ ለመጠየቅ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን የተጠቀመ እንደሆነ 100 ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣት እና ከ7 ዓመት እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

II. በተራ ቁጥር የተጠቀሱትን የተጭበረበሩ ደረሰኞች በመጠቀም የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ከ100 ሺህ ብር የሚበልጥ እንደሆነ፣ የሚጣለው ቅጣት ከገንዘቡ ጥቅም ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ ቅጣት እና ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደረስ ጽኑ እስራት ይሆናል።

III. ሀሰተኛ ደረሰኞችን ለመሥራት፣ ለማዘጋጀት ወይም ለማተም የሚያገለግል ማሽን፣ መሣሪያ ወይም ሶፍትዌር የያዘ፣ የሸጠ፣ ያከራየ ወይም በሌላ መንገድ ያቀረበ ማንኛውም ሰው በ200 ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣት እና ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

የወንጀል ቅጣት...

IV. በተራ ቁጥር (III) መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ መገኘት ማሽኑን፣ መሣሪያውን፣ ሶፍትዌሩን ወይም የወንጀሉን ፍሬ መውረስን ያስከትላል።

V. ሀሰተኛ ደረሰኞችን የያዘ፣ ያስቀመጠ፣ ለሽያጭ ያመቻቸ ወይም ሀሰተኛ ደረሰኞች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ ሰው ከ3 ዓመት እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

VI. ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ከ25ሺ እስከ 50ሺ ብር እና ከ3-5 ዓመት ጽኑ እስራት ይቀጣል።

የወንጀል ቅጣት...

vII. በአንድ ግብይት በተሰጡ ተመሳሳይ የደረሰኝ ኮፒዎች ላይ የተለያዩ ዋጋዎችን በመመዝገብ የሸያጭ ዋጋን ያሳነሰ በብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ብር እና ከ5 ዓመት እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

vIII. ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ የሰጠ/የተቀበለ ሰው ከ100 ሺህ-200 ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣት እና ከ7-10 ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት።

Ix. በተራ ቁጥር vIII የተመለከተው ደረሰኝ ከ200 ሺህ የሚበልጥ የገንዘብ መጠን የያዘ እንደሆነ በዚህ ተራ ቁጥር vI መሠረት የሚጣለው ቅጣት በደረሰኙ ከተገለጸው የገንዘብ መጠን ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ ቅጣት እና ከ10 እስከ 15 ዓመት የሚደረስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

የወንጀል ቅጣት...

X. ሳይፈቅድለት የታክስ ደረሰኝ ያተመ ሰው ከ300 መቶ ሺህ - 500 መቶ ሺህ ብር እና ከ2-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

XI. በተራ ቁጥር (X) መሠረት ጥፋተኛ የተባለ ሰው ወንጀሉን ለሁለተኛ ጊዜ ፈፅሞ ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ የህትመት መሣሪያው እና የማተሚያ ድርጅቱ ይወረሳል፣ የንግድ ፈቃዱም ይሰረዛል።



ሙከራ ሶስት

- በደረሰኝ ዙሪያ በአዋጅ እና በመመሪያ የተደነገጉ ጉዳዮች ቢጣሱ ከሚያስከትሉት የቅጣት ወንጀሎች ሁለቱን ግለጹ?

ክፍል ሶስት:- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ

3.1. <u>የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ምንድንነው?</u>

- በሽያጭ መደበኛ ደረሰኝ ፋንታ የሸቀጦችን ወይም የአገልግሎቶችን ሽያጭ የሚመዘግብና ለማንበብ ብቻ የሚቻል ማስታወሻን የሚያከማች በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ፕሮግራም የሚደረግ ቺፕ የተገጠመበት በሰርክዩት የተጋገረ ፕሮግራም የሚጠቀም መሳሪያ ነው።
- በንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄዱ የዕለት ተዕለት የዕቃ ሽያጭና አገልግሎት ግብይቶችን እየመዘገበ፣ ኤልክትሮኒክስ ደረሰኝ እያተመ የሚያወጣ እና ከዋና የመረጃ ቋት ጋር የተገናኘ መሳሪያ ነው።

3.2 የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ዓይነቶች


- **የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያ (sales registor machine):-** ማለት በሽያጭ መደበኛ ደረሰኝ ፋንታ የዕቃዎችን ወይም የአገልግሎቶችን ሽያጭ የሚመዘግብና ለማንበብ ብቻ የሚቻል ማስታወሻን የሚያከማች በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ፕሮግራም የሚደረግ (ቺፕ) የተገጠመለት በሰርኪዩት የተጋገረ ፕሮግራም የሚጠቀም መሣሪያ ነው።

-  ኝ ራሱን ችሎ የሚሠራ።



➢ የሽያጭ ነቁጣ መሳሪያ(point of sale)

- **የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ፡-**ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚተካ ኮምፒዩተራይዝድ የሆነ መሣሪያ ሲሆን የደንበኞቻችን ትዕዛዝ፣ የትዕዛዙን አፈፃፀምና ሂደትና፣ የዴቢትና ክሬዲት ካርድ ሂሳብን የመመዝገብና የመቆጣጠርና የመሰሰሉትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ተጨማሪ አቅም ያለው መሣሪያ ነው።



3.3 ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ታትመው የሚወጡ ሰነዶች

- **የፊሲካል ሰነዶች:-**


- የፊስካል እና የተመላሽ ደረሰኝ፣
- የዕለታዊ የሽያጭ ማጠቃለያ ሪፖርት /Z-Report/፣
- የማጠቃለያ ሪፖርት /Summary Report/።

ታትመው የሚወጡ ሰነዶች....

❑ ፊሲካል ያልሆኑ ሰነዶች

በማናቸውም ሁኔታ ለተሸጠ እቃ ወይም ለተሰጠ አገልግሎት እንደ ማስረጃ ሆኖ ሊያገለግል የማይችል ሲሆን ‘NON FISCAL’ የሚለው ፅሁፍ በሰነዶቹ ራስጌ፣ መሀከል እና ግርጌ ላይ መታተም አለበት

- ኤክስ ሪፖርት /X-Report/፣
- የተሸጡ ዕቃዎች ዝርዝር /PLU Report/
- የወጥ ቤት ትዕዛዝ /Kitchen Order/


1234567890
ABEBE KEBEDE AYELE
ABE GEROSERY
A.A BOLE K.K WO.04 H.No 12
Abebe Aregay Street
TEL. 011647902
NON FISCAL
NF. No.00000045
21/02/2013 14:30
R/A CASH *5,000.00
NON FISCAL

R/A CASH *5,000.00
NON FISCAL

3.4 የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ጥቅሞች

➢ ከግብር ከፋዩ አንፃር

- ❑ ሻጭ ድርጅቶች እስቶካቸውን ለማወቅና ለመቆጣጠር ይረዳቸዋል፤
- ❑ በሽያጭ ሠራተኞችና በድርጅቱ መካከል መተማመንን ያጠናክራል፤
- ❑ ፍትሐዊ የግብር ውሳኔ እንዲከናወን ያግዛል፤
- ❑ ጤናማ የገበያ ውድድር እንዲኖር ያደርጋል
- ❑ ገዢዎች የሚከፍሉት ታክስ በትክክል ለመንግሥት ገቢ ለመደረጉ እርግጠኝነት ይሰማቸዋል።
- ❑ ዘመናዊ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ እንዲኖር ያደርጋል
- ❑ ደረሰኝ በእጅ ለማዘጋጀት የሚወስደውን ጊዜ ይቀንሳል፤

ከግብር ሰብሳቢ ባለሥልጣኑ አንጻር

- ፍትሃዊ የግብር አሰባሰብ ሥርዓትን ለማስፈን ይረዳል፣
- በመረጃ ላይ የተመሰረተ የግብር አሰባሰብ ሥርዓትን ለማስፈን ይረዳል፣
- ወቅታዊ የሸያጭ መረጃ እንዲኖረው ያደርጋል
- ከግብር ከፋዮች ማህበረሰብ በእምነት ላይ የተመሰረተ የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል::
- ለታክስ ውሳኔ የሚረዱ መረጃዎችን በአጭር ጊዜ ለማግኘት ያስችላል፤
- ዘመናዊ መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት በማስፈን ህገ ወጥነት ለመከላከል ያስችላል፤



መከራ አራት

1. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ምንድን ነው ጠቀሜታውስ?

2. የሽ/መ/መሳሪያ መጠቀም ያለባቸው እነማን ናቸው? የማይገደዱትስ?

3.5 የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ መጠቀም ያለባቸው እነማን ናቸው?

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን ስለመጠቀም ባወጣው ደንብ ቁጥር 139/99መሰረት ባለሥልጣኑ ግዴታ የሚጥልባቸው ማናቸውም የደረጃ “ሀ” እና የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች በሽ/መ/መሳሪያ መጠቀም ይኖርባቸዋል።

3.6 የሽ.መ.መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ የሌለባቸው

- ከ500ሺ ብር በታች ዓመታዊ ገቢ ያላቸው ድርጅቶችና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች፣
- የቤት ኪራይ ገቢ የሚያገኙ ግብር ከፋዮች፣
- ጠበቆችና ወይም አማካሪዎች፣ ላኪዎች፣
- ሥዕል ወይም የቅርፃ ቅርጽ ሥራ የሚሠሩ፣
- የአምቡላንስ አገልግሎት የሚሰጡ፣
- የቤት ለቤት ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ፣
- በእርሻ ሥራ የተሠማሩ፣
- ለብሔራዊ ባንክ ወርቅ የሚያቀርቡ
- በምርት ገበያ ማዕከል በኩል የሚገበያዩ ግብር ከፋዮች

3.7 የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ለመግዛት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

- በዘመኑ የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሰርተፍኬት፣
- ድርጅቱ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰርተፊኬት፣
- ደረጃ 'ለ' ታክስ ተመዝጋቢ ከሆነ ደብዳቤ ለአቅራቢ ድርጅት ማረጋገጫ ማቅረብ።

3.8 የሽ.መ.መሳሪያ ተጠቃሚዎች ማወቅ የሚገባቸው ነገሮች

- እውቅና ያልተሰጠው/ያልተመዘገበ የሽ.መ.መሳሪያ አለመጠቀም::
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ከተርሚናል ጋር አለማለያየት።
- መሣሪያው ብልሽት ቢያጋጥመውና ተጠቃሚው ሳይሰብር ሊያስተካክለው የማይችል ከሆነ መጠቀሙን ወዲያውኑ አቋርጦ ብልሽቱ ያጋጠመበትን ጊዜ በምርመራ መዝገቡ ላይ መመዝገብና በ2 ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑና ለአገልግሎት ማዕከሉ በስልክ ማስታወቅ።
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን የምርመራ መዝገብ ከመሣሪያው ጐን ማስቀመጥ

ማወቅ የሚገባቸው ነገሮች...

- የተበላሸው መሣሪያ እስከሚስተካከል ወይም በሌላ መሣሪያ እስከሚተካ ተጠቃሚው በባለሥልጣኑ ፈቃድ በታተመ ደረሰኝ ግብይቱን ማከናወን አለበት። ሆኖም በታተመ ደረሰኝ ግብይት ማከናወን የሚችለው በ1 ዓመት ውስጥ ከ5 ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ ብቻ ይሆናል።
- የመሣሪያው የባለቤትነት መብት ለሌላ ሰው/ድርጅት የተላለፈ እንደሆነ ቀደም ሲል የመሣሪያው ባለቤት የነበረው ሰው/ድርጅት ይጠቀምበት የነበረው የፊሲካል ማስታወሻ ከመሣሪያው እንዲወጣ ተደርጎ በአዲስ ይተካል

ማወቅ የሚገባቸው ነገሮች...

- የባለቤትነት ለውጥ ሲደረግ መሣሪያውን የገዛው ሰው ከተመዘገበ የአገልግሎት ማዕከል ጋር ውለታ መግባት ያለበት ሲሆን መሣሪያውንም በባለሥልጣኑ ዘንድ ማስመዝገብ አለበት።

- ሶስቱን ማስታወቂያዎች ማለትም፦

  - የተጠቃሚውን ስም (የንግድ ስም፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ዕውቅና እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር)።
  - “ደረሰኝ የማይሰጥ ከሆነ አይክፈሉ” የሚል ፅሑፍ፣
  - የሽያጭ ሠራተኛ መሣሪያው የተበላሸ ከሆነ በባለሥልጣኑ (ገቢዎች ሚኒስቴር) ፈቃድ የታተመ ተከታታይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ ለደንበኛው የመስጠት ግዴታ አለበት የሚል ማስታወቅያ መለጠፍ አለበት

3.9 የአቅራቢ ግዴታዎች

- የመሣሪያው አቅራቢ፤ መሣሪያውን ከውጪ ለማስገባትና አቅርቦት ከመጀመሩ በፊት እውቅና ከባለሥልጣኑ ሊያገኝ ይገባል።
- አቅራቢው የቴክኒክ እውቀት ባላቸው ሠራተኞችና በበቂ የመለዋወጫ መሣሪያዎች የተሟላ የጥገና መስጫ ማዕከላትን ማደራጀት
- የመሣሪያው ተጠቃሚ የመሣሪያዎቹን ጥገና እና እድሳት አገልግሎት እንዲያገኙ የማድረግ ግዴታ አለበት፤
- ለመሣሪያው ተጠቃሚ ሠራተኞች ስለመሣሪያዎቹ አጠቃቀም ሥልጠና የመስጠት ግዴታ አለበት፤
- የመሣሪያዎቹን መለዋወጫ እስከ 5 ዓመት ድረስ የመያዝ ግዴታ አለበት፤
- አቅራቢው የመሣሪያዎች ብልሽት በተገለጸለት በ48 ሰዓት ውስጥ የጥገና አገልግሎት መስጠት አለበት።
- በሥራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ላይ የሚደረገውን ማናቸውንም ለውጥ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት

3.10 ተንቀሳቃሽ ሸያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ

- ተንቀሳቃሽ ሸያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚጠቀሙ ግብር ከፋዮች በየዘርፋቸው ተለይተው ማሽኑን እንቀሳቅሰው እንዲጠቀሙ በታመነበት የንግድ ሥራ ዓይነት ላይ የተሠማሩ መሆን አለባቸው።
- ሸያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ለማንቀሳቀስ የሚችሉት ደረሰኝ ለመቁረጥ ብቻ በመሆኑ ደረሰኝ ከተቆረጠ በኋላ ማሽኑ ለሥራ በተዘጋጀበት የንግድ ፈቃድ አድራሻ ተመልሶ መተከል ይኖርበታል።

3.11 የአድራሻ ለውጥ ለማድረግ መሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

- በአዲሱ የንግድ አድራሻ የተቀየረ የንግድ ምዝገባ ፈቃድ እና የንግድ ፈቃድ፣
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ካላቸው ማቅረብ አለባቸው።
- ለታክስ ባለሥልጣኑ የአድራሻ ለውጥን ማሳወቅ፣
- የአድራሻ ለውጥ ለማድረግ የሚያስችል ከግብር ከፋዩ የንግድ ማዕከል የተጻፈ የአድራሻ ለውጥ ደብዳቤ ለአቅራቢው መውሰድ፤

3.12 የሽ.መ.መ. በአደራ የሚቀመጥባቸው ሁኔታዎች እና መሟላት ያለባቸው ነገሮች

- በልማት ምክንያት የንግድ ቤት ሲፈርስ፤
  - የፈረሰ መሆኑን ከሚመለከተው አካል ደብዳቤ ማቅረብ፣
  - ለአቅራቢው ማሽኑ በአደራ እንዲቀመጥ ከግብር ከፋዩ የግብር ማዕከል የተፃፈ ደብዳቤ መውሰድ፣
  - የተሰጠው ጊዜ ከማለቁ በፊት ተለዋጭ የንግድ አድረሻ ማግኘት ካልተቻለ የተሰጠው ጊዜ ከማለቁ በፊት ለግብር ማዕከሉ ማሳወቅ፣

አደራ ማስቀመጥ.....

የቤት ኪራይ ውል ሲቋረጥ

- ከውልና ማስረጃ ደብዳቤ ማቅረብ፣
- ለአቅራቢው ማሽኑ በአደራ እንዲቀመጥ ከግብር ከፋዩ የግብር ማዕከል የተጻፈ ደብዳቤ መውሰድ፣
- ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ተለዋጭ የንግድ አድራሻ ማግኘት ካልተቻለ የተሰጠው ጊዜ ከማለቁ በፊት ለዋናው መ/ቤት ቀርበው ያለውን ችግር ማመልከት እና ውሳኔ እንዲያገኝ ማድረግ፣

አደራ ማስቀመጥ ...

- **የንግድ ድርጅትን ለመዝጋት በአዲት ላይ ሲሆን፤**

  - የንግድ ፈቃድ አውጥቶ ሲሠራበት የነበረውን የንግድ ድርጅት ለማዘጋት በግብር ማዕከሉ ላለ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ማቅረብ፤
  - የንግድ ድርጅቱን ለመዝጋት ያመለከተ መሆኑን የሚገልፅና ከደንበኞች አገልግሎት የተጻፈ ደብዳቤ በግብር ማዕከሉ ላለ ለሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ቡድን ማቅረብ፤
  - የንግድ ድርጅቱን ለመዝጋት አዲት ላይ መሆኑን ተገልጾ ሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው በአደራ እንዲቀመጥ በግብር ማዕከሉ ካለ ሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ቡድን ደብዳቤ ለአቅራቢው መጻፍ።

3.13 የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የባለቤት ለውጥ

- አንድ ግብር ከፋይ ይጠቀምበት የነበረውን የሽያጭ መዝገቢያ መሣሪያ የባለቤት ለውጥ በማድረግ ወደ ሌላ ተጠቃሚ ማዘዋወር ሲፈለግ:-
  - ✓ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ተመላሽ የተደረገበትን ደብዳቤ
  - ✓ ከአንድ በላይ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ መኖሩ ከታወቀ ይህንን የሚያሳይ ማስረጃ፤
  - ✓ የንግድ ፍቃድና የንግድ ምዝገባ ሰርተፊኬት ማቅረብ፤
  - ✓ አስተላላፊውና የሚተላለፍለት ግብር ከፋይ /አዲሱ ተጠቃሚ/ መስማማታቸውን የሚያሳይ ለየብቻ በእያንዳንዳቸው የተጻፈ ደብዳቤ ከሙሉ መረጃቸው ጋር በማመልከቻ ለግብር ማዕከሉ ማቅረብ ይኖርባቸዋል

3.14 የሽያጭ ማጠቃለያ ሪፖርት በየቀኑ ማውጣት ስለማይጠበቅባቸው የንግድ መስኮች

- የንግድ ባሕሪያቸው ተጠንቶ በየቀኑ ግብይት የሌላቸው ግብር ከፋዮች በሚል የተለዩ ግብር ከፋዮች ሽያጭ በተከናወነ ቁጥር የሚወጣው ዜድ ሪፖርት እንደተጠበቀ ሆኖ ታክሱን ሲያሳውቁ የወሩን የመጀመሪያ ቀን እና የወሩን የመጨረሻ ቀን የየወቅቱን ሽያጭ ማጠቃለያ በማውጣት ከማስታወቂያ ቅጹ ጋር ግብር ለሚከፍሉበት ቅርንጫፍ ማቅረብ አለባቸው ።

- የወሩ የመጨረሻ ቀን ስራ በማይሰራበት የእረፍት ወይም የህዝብ በዓላት ቀን ላይ የሚውል በሆነ ጊዜ ዜድ ሪፖርት አስቀድሞ ባለው የስራ ቀን መውጣት አለበት

3.15. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን ስለማስወገድ

3.15.1.የሽ/መ/መሳሪያ የሚወገድባቸው ምክንያቶች

- ✓ ተጠቃሚው የንግድ ስራውን በጊዜያዊነት ሲያቆም ወይም ድርጅቱ ሙሉ ለሙሉ ሲዘጋ
- ✓ መሳሪያው በሌላ ሲተካ ወይንም ሲቀየር
- ✓ መሳሪው ሲበላሽ ወይንም መለዋወጫ ሊገኝለት የማይችል ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ

3.15.2 የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚወገድባቸው ሁኔታዎች

- ለሌላ ተጠቃሚ በሽያጭ ወይንም በስጦታ በማስተላለፍ
- ለአቅራቢው ወይም አገልግሎት ማዕከሉ በመሸጥ
- በሽያጭ ሊወገዱ የማይችሉ ወይም የእርጅና ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ያልተወገዱትን መሳሪያዎች ያለምንም ዋጋ ለባለስልጣኑ በማስረከብ



ሙከራ አምስት

1. የሽ/መ/መሳሪያ በአደራ የሚቀመጥባቸው ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?
2. የሽ/መ/መሳሪያ ተጠቃሚዎች ማድረግ ያለባቸው(ማወቅ ካለባቸው) ነገሮች ውስጥ 3ቱን ጥቀስ?
3. የሽ/መ/መሳሪያ የሚወገድባቸው ሁኔታዎች(መንገዶች) ምን ምን ናቸው?

3.16. ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ጋር ተያይዞ የሚጣል ቅጣት

- ተጠቃሚው

✓ እውቅና ያልተሰጠው መሣሪያ ወይም ሶፍትዌር የተጠቀመ ለእያንዳንዱ መሣሪያ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር)

✓ በበቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ደረሰኝ ውጪ ግብይት ካከናወነ 50,000 (ሃምሳ ሺ ብር)

✓ በመሳሪያው ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊሲካል ማስታወሻ እንዲቀየር ያደረገ ብር 100000.00 (አንድ መቶ ሺ ብር)

✓ የታክስ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ሥርዓት አዲት እንዳያደርግ መሰናክል የፈጠረ ወይም አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ያላደረገ ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺ ብር)

ቅጣት.....

- ✓ ከአገልግሎት ማዕከል ጋር ውል ካልፈጸመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ከተርሚናል ጋር ሳያያይዝ ከተጠቀመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የምርመራ መዝገብ ከመሣሪያው ጐን እንዲቀመጥ ካላደረገ ወይም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የተመዘገቡ ዕቃዎች ተመላሽ መደረጋቸው ወይም ደንበኛው የተመላሽ ጥያቄ ማቅረቡ በተመላሽ መዝገብ ሳይ በትክክል መመዘገቡ ሳይረጋገጥ የተመላሽ ደረሰኝ ከሰጠ ብር **25,000.00** (ሃያ አምስት ብር) ቅጣት ይከፍላል።
- ✓ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው አገልግሎት መስጠት ሲያቋርጥ በሦስት ቀናት ውስጥ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ብልሽት ባጋጠመው በአራት ሰዓት ውስጥ ለአገልግሎት ማዕከሉ እና ለባለሥልጣኑ ካላሳወቀ ብር 10,000.00 (አስር ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል።
- ✓ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚቀመጥበትን የንግድ ቦታ ትክክለኛ አድራሻ ለባለሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል።

ቅጣት.....

- ✓ የአድራሻ ወይም የስም ለውጥ ሲያደርግ ወይም የንግድ ሥራውን የሚያቋርጥ ሲሆን ሦስት ቀናት አስቀድሞ ለአገልግሎት ማዕከሉ እና ለባለሥልጣኑ ያላሳወቀ እንደሆነ ብር 25,000.0 (ሃያ አምስት ሺ ብር)
- ✓ በንግድ ሥራ ቦታው:-
  - የተጠቃሚውን ስም፣ የንግድ ስም፣ የንግዱ ሥራ የሚካሄድበትን አድራሻ፣ የታክስ ከፋዩን መለያ ቁጥር፣ የሽያጭ መመዝገቢያውን ዕውቅና እና መጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፣
  - "የሽያጭ ሠራተኞች መሣሪያው የተበላሸ ከሆነ በባለሥልጣኑ ፈቃድ የታተመ ተከታታይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ ለደንበኞች የመስጠት ግዴታ አለባቸው" የሚል ማስታወቂያ፣ እና
  - "ደረሰኝ የማይሰጥ ከሆነ አይክፈሉ" የሚል ጽሑፍ ያለበት ማስታወቂያ፣ በግልፅና በሚታይ ቦታ ለጥፎ ካልተገኘ ብር 10,000.00 (አስር ሺ ብር)
- ✓ ዕውቅና ባልተሰጠው ሰው ሶፍትዌር እንዲቀየር ወይም እንዲሻሻል ካደረገ ብር 30,000.00 (ሠላሳ ሺ ብር)

ቅጣት.....

- አቅራቢው

✓ የንግድ ሥራውን የአድራሻ ለውጥ ለባለሥልጣኑ ካላሳወቀ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል።

✓ በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ለገበያ ካዋለ ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል።

✓ ለእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ምዝገባ ከባለሥልጣኑ የመሣሪያ መለያ ቁጥር ካልወሰደ ወይም የወሰደውን የመሣሪያ መለያ ቁጥር ለዕይታ በሚያመች ቦታ በመሣሪያው ላይ ካለጠፈ ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺ ብር) ቅጣት ይከፍላል።

ቅጣት.....

- ✓ በማሽኑ ላይ የሚያደርገውን ማናቸውንም ለውጥ ለባለሥልጣኑ በቅድሚያ ካላሳወቀ ወይም ስለ መሣሪያው አጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺ ብር)
- ✓ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በመሰረቃቸው ወይም ሊጠገኑ በማይቻልበት ሁኔታ በአደጋ ምክንያት ብልሽት የደረሰባቸው መሆኑን አስታውቀው እንዲተኩላቸው ለሚጠይቁ አገልግሎት ማዕከላት በሦስት ቀናት ውስጥ ለማቅረብ አለመቻሉን ለባለሥልጣኑ አስቀድሞ ካላሳወቀ ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺ ብር)
- ✓ ውል ስለተዋዋላቸው አገልግሎት ማዕከላት መረጃ ካልያዘ ወይም ውላቸውን ስላቋረጡ ወይም አዲስ ስለተዋዋላቸው የአገልግሎት ማዕከላት ለባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺ ብር)

ቅጣት.....

- የአገልግሎት ማዕከል
  - ✓ የፊሲካል ማስታወሻ በተተካ በሁለት ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ካላሳወቀ ብር **20,000.00 (ሃያ ሺ ብር)**
  - ✓ ውል የገባባቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በዓመት አንድ ጊዜ የቴክኒክ ምርመራ ካላደረገ ብር **20,000.00 (ሃያ ሺ ብር)**
  - ✓ አቅራቢው ዕውቅና ሳይሰጠው እና በባለሥልጣኑ ሳይመዘገብ በሥራ ላሠማራው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ብር **50,000.00 (ሃምሳ ሺ ብር)** ቅጣት ይከፍላል።

3.16 ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ጋር ተያይዞ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ቅጣት

- ተጠቃሚው፤

- ዕውቅና ያልተሰጠው/ያልተመዘገበ የሽ.መ.መሳሪያ ከተጠቀመ ከ3 ዓመት በማያንስ እና ከ7 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤
- መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ/በሌላ በቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በሽ.መ.መሳሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ከ2 ዓመት በማያንስ እና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤
- የፊሲካል ማስታወሻ እንዲቀየር ያደረገ /ጉዳት ያደረሰ/ ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ ከ3 ዓመት በማያንስ እና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት

- **አቅራቢው፤**
  - በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠውን መሣሪያ/ሶፍትዌር ለገበያ ካዋለ ከ3 ዓመት በማያንስ እና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት፤
  - በሥራ ላይ ባሉ የሽ.መ.መሣሪያዎች ላይ የሚደረገውን ማናቸውንም ለውጥ በቅድሚያ ካላስታወቀ/በመሣሪያው አጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ/ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ ከ3 ዓመት በማያንስ እና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።
- ማንኛውም ሰው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ፈቃድ ሳይኖረው ማንኛውንም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም ሶፍትዌር ለገበያ ያዋለ እንደሆነ ከ5 ዓመት እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ያስቀጣል

የአገልግሎት ማዕከል

አቅራቢው ዕውቅና ያልሰጠውን እና በባለሥልጣኑ ያልተመዘገበ ሠራተኛ በሥራ ላይ አሰማርቶ ከተገኘ 50 ሺ ብር ወይም ከ1 ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ያስቀጣል፤

የአገልግሎት ማዕከል ሠራተኛ

- የሸ.መ.መ. ያለአገልግሎት ማዕከሉ እና ባለሥልጣኑ ዕውቅና ከፈታታ/ከገጣጠመ/
- የሸ.መ.መሳሪያው ሳይበላሽ ሆን ብሎ እሸጉን ካነሳ ወይም አካሉን ከቀየረ ከ10 ሺ ብር በማይበልጥ ቅጣት እና ከ1 ዓመት በማያንስ እና ከ3 ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል፤

❑ የታክስ ሰራተኛው

- የሽ.መ.መሳሪያውን የፈታ/የገጣጠመ/
- የአገልግሎት ማዕከል ሠራተኛ በሌለበት ሥራ ላይ እንዲውል የፈቀደ
- የመሣሪያውን መለያ ቁጥር የቀያየረ እንደሆነ፣
- በሽ.መ.መሳሪያ ተጠቃሚው /በአገልግሎት ማዕከሉ /በሠራተኛው/ በአቅራቢው/ የተፈፀመ ማናቸውንም ሕገ ወጥ ድርጊት እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በ24 ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ ከ5 ሺ ብር በማይበልጥ ቅጣት እና ከ1 ዓመት በማያንስ እና ከ3 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።



ሙከራ ስድስት

1.ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪዎች ጋር በተገናኘ በተጠቃሚው የሚፈጸሙ ወንጀሎችን አብራሩ?

የደረሰኝ እና የሽያጭ መመዝገቢያ አጠቃቀም ሕጉን መከተል ጠቀሜታው የጎላ ሲሆን ያለደረሰኝ ግብይት ማከናወን እንዲሁም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን በታክስ ሕጉ መሠረት አለመጠቀም አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶችን የሚያስከትል ይሆናል።

ማጣቀሻ

- የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008
- የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን ስለመጠቀም ግዴታ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/96
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 46/99ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 87/2005
- Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Tax Administration Proclamation No. 983/2016 Technical Notes


እመጣለሁ!
ኢሜይል፡-
morethiopia@gmail.com
ዩቲዩብ፡-
mor taxpayer education